
# <u>ሰዋስወ ግእዝ</u>

ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፈ ሰዋስው ዘግእዝ በዓመተ ሢመተ ፓትርያርክነቱ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፤ ፓትርያርክ ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፡ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ።



<u>አሳታሚ</u>
ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
አዲስ አበባ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ
ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት

<u>መ ግ ለ ጫ</u>

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት ፣ በኋላም በሕገ ወንጌል አምና የምትኖር ጥንታዊት ሀገር ናት።

ቀደም ሲል የነበረው አሁንም ያለው የሕዝቧ ሥልጣኔ፤ ጀግንነቱ፣ እምነቱና ባህሉ በዓለም ሁሉ ሊታወቅ የቻለው በድንጋይ ሐውልቶች፣ በሸክላ ዕቃዎችና በብራና ፣ በግእዝ ቋንቋ ተጽፈውና ተሥለው ከትውልደ–ትውልድ እየተላለፉ በመጡት ቅርሶቿ ነው።

በግእዝ ቋንቋ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፣ ብዙ ቅኔዎችና ድርሰቶችም ተደርሰዋል። የሀገራችንና የቤተክርስቲያናችንም ታሪክ ለትውልደ–ትውልድ ሊደርሱ የቻሉት በግእዝ ቋንቋ በብራናና በወረቀት ተጽፈው በሚገኙት መጻሕፍት ነው። እስከ አሁንም ድረስ ተተርጉመው ለሕዝብ ያልቀረቡና በየገዳማቱ ተጠብቀው የሚገኙ የእምነት ፣ የሥነ ምግባር፣ የታሪክ፣ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸው። በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት፣ ለመመርመርና ለመተርጐም ጠለቅ ያለ የግእዝ ሰዋሰው ዕውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

የግእዝ ቋንቋ፣ አማርኛ በቦታው እስከተተካበት ማለትም እስከ ፲፪ኛው ምዕት ዓመት የሀገሪቱ ሥርዓተ መንግሥት የሚመራበት ፣ ሕብረተሰቡ በጽሑፍም ሆነ በቃል አሳቡን የሚገልጥበት ፣ የእፍ መፍቻ ፣ የምሥጢራት መክፈቻ ፤ የሰዋስው መግቻ ሆኖ የቆየ ቋንቋ ከመሆኑም በላይ በሰዋስው ረገድም የአማርኛው ቋንቋ መቶ በመቶ የግእዙን ሥርዓት የተከተለ ነው።

የግእዝ ቋንቋ እጅግ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ የውጭ ቋንቋዎች በሚተረጉሙበት ጊዜ በአማርኛውም ሆነ በሌሎች የብሔረሰብ ቋንቋዎች ቃላት ያልተገኘላቸው በግእዙ እየተገኘላቸው ሊተረጐሙ እንደቻሉ ከዚህ በፊት በተደረገው የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጊዜ በሥራ ላይ ውሏል። ለምሳሌ በውጭ ቃላት " ሚልክ–ዌይ" ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲተረጎም ፍኖተ ሀሊብ ፤ "ቴሌስኮፕ" መቅርበ–ኮከብ " ግራቪቲ" ስህበተ–ምድር፤ "ማግኔት "ምስሐበ–ብርት፣ "አይዲኦሎጂ" ርእዮተ ዓለም፤ " ኤቫፖሬሽን" ተን፤ "ኮምፓውንድ " ውሑድ…ወዘተ እየተባለ ተተርጉሞአል። በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የግእዝ ቋንቋ ጠቃሚነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። እስከ አሁንም በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ሕያው ሆኖ ኖሮአል። በብሔራዊ ደረጃ ለአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናም እየቀረበም ነው። በውጭውም ዓለም በብዙ ዩንቨርስቲዎች የግእዝ ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል።

እንግዲህ ግእዝ አእምሮን ለማዳበር፣ የእውቀትን አድማስ ለማስፋትና ለምርምር ከመጥቀሙም በላይ ለአያሌ የአገሪቱ ቋንቋዎች መሠረትና ምንጭ ስለሆነ ብዙዎች ሊማሩትና ሊያውቁት እንደሚገባ በማመን ከጥንት አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ይህንን " ሰዋስወ – ግእዝ" የተሰኘውን መጽሐፍ አሳትመን ማቅረባችንን ለአንባብያንና ሙያውን ለሚሹ ስናበስር መንፈሳዊ ደስታ ያሰማናል። " በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" ተብሏልና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ማሳተሚያ ድርጅቱ

ቈቋዕያን ፡ ቈቋዒት ፡ ቈቋዕያት ፡ ቀኊዖ ፡ ቈቋዒ ፡ ቀኊቋዔ ፡ ነው ።

ጐድአ ፡ ሲረባ ፡ ጐድአ ፡ ይጐድእ ፡ ይጐዳእ ፡ ይጐዳእ ፡ ጐዲእ ፡ ጐዲአት ፡ ጐዳኢ ፡ ጐዳእያን ፡ ጐዳኢት ፡ ጐዳእያት ፡ ጐዱእ ፡ ጐዳኢ ፡ መጐድእ ፡ ነው ።

ጐሕቈ ፡ ሲረባ ፡ ጐሕቈ ፡ ይጐሕቊ ፡ ይጐሐቊ ፡ ይጐሐቊ ፡ ጐሒቊ ፡ ጐሒቈት ፡ ጐሐቊ ፡ ጐሐቊያን ፡ ጐሐቊት ፡ ጐሐቊያት ፡ ጐሑቊ ፡ ጐሐቊ ፡ ነው ።

ጐንደየ ፡ ሲረባ ፡ ጐንደየ ፡ ይጐንዲ ፡ ይጐንዲ ፡ ይጐንዲ ፡ ጐንድዮ ፡ ጐንድዮት ፡ ጐንዳዪ ፡ ጐንዳይያን ፡ ጐንዳዪት ፡ ጐንዳይያት ፡ ጐንዱይ ፡ ጐንዳዪ ።

ጐየ ፡ ሲረባ ፡ ጐየ ፡ ይጐዪይ ፡ ይጐየይ ፡ ይጐየይ ፡ ጐይዮ ፡ ጐዪዮት ፡ ጐያዪ ፡ ጐያዪያን ጐያዪት ፡ ጐያዪያት ፡ ጐዩት ።

በዝየ ፡ ተፈጸመ ፡ አርባ ፡ ቅምር ፡ ሺወ፰ ፡ ክፍል ።